ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ

በየካቲት 26 ቀን 2010 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ጋጋታ ፤ የሕዝቡን ዐመፅ አይገታውም !
## በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የታወጀው ጦርነት ብርቱ ተቃውሞ ገጥሞታል !

የሀገራችን ሕዝብ ለአለፋት ሃያ ስድስት ዐመታት የተጫነበትን አንገፍጋፊ ዘረኛ አገዛዝ በመቃወም ከዳር እስከዳር ወሳኝ ትግል እያከሄደ፤ አይከፍሉ መሥዋዕት ሲከፍል ቆይቷል ።በርካታ የሕዝብ ወገኖች፤ ሀገር ወዳድ ታጋዮች፤ የጎሊና እስረኞች፤ የሃይማኖት አባቶች፤ ወጣቶችና አዛውንት መሥዋዕት በመክፈል፤ ሁሉም ግዴታቸውን ተወጥተዋል ። የሀገርና የወገን ፍቅር ውድ ዋጋ እንደሚያስከፍል በተግባር አስመስክረዋል ። መዳረሻቸው በትክክል የልታወቀ የሀገሪቱ ብርቅ ልጆች አስታዋሽ አጥተው ቀርተዋል። ፍለጋው ግን እንደቀጠለ ነው። የእነርሱ ሁነኛ መዳረሻ እስከልታወቀ ድረስ ትግሉ አይቆምም።

በአሁኑ ወቅት፤ ሕዝባዊው አመፅ ማንም ኃይል ሊያቆመው ቀርቶ ሊገታውና አቅጣጫውንም ሊያስለውጠው ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል። ቀልባሹቹ ይቀለበሳሉ እንጅ ዐመፁ አይቀለበስም። የዐመፁን ስፋትና ከፍታ፤ ግለትና ቱማታ፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንኳ በምኞት ደረጃ ካልሆነ በስተቀር፤ እስከዚህም ድረስ፤ መሬት አንቀጥቃጭና ጠላት አርበትባች ይሆናል ብሎ አልተገመተም ቢባል ፤ስህተት አይሆንም። አሁን ግን፤ አብዛኛው ሊገምተው ከማይችልበት ደረጃ በላይ አልፏል ።ይኽ ሕዝባዊ ዕመፅ ፤የማዕበልና የነበልባል ባኅርይን ተላብሶ በመላው ሀገሪቱ፤ እንደ መንጠር ዕሳት እየተቀጣጠለ ፤ እንደ ጥፋት ወሃ እየተመመ ፤ የኢትዮጵያን ጠላቶች እያርበተበተ ይገኛል። በሕዝባዊው ዐመጽ በድል ካልተጠንቀቀ መቆሚያ የለውም። ያስቸኳይ ዐዋጅ ጋጋታ፤ የተርበትባቾች ሁካታ፤ የዘረኞች ጫጫታ የሕዝቡን ዐመፅ አይገታውም ።

መግቢያ መውጫ የተሳነው ይኽ ዘረኛ አገዛዝ፤ ሕይወቱን ያቆየ መስሎት፤ በሕዝቡ ላይ አስቸኳይ ዐዋጅ ልፍፏል። ጦርነት አውጇል ። ማዘዣ ጣቢያዎችን / ኮማንድ ፖስት አቋቁሟል። ሰዓት ዕላፊ

ወስኗል። የመግደያ ቦታዎችን አዘጋጅቷል። ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በይበልጥ አፍኗል። ዕመቃውን አጠናክሯል። ነፍሰ ገዳዮቹን በየቦታው አስፍሯል። የጅምላ ግድያ እንዲፈጽሙ ቋሚ ትዕዛዝ አስተላልፏል። **ለመግደል ብቻ ተኩስ ! በጅምላ እያፈስክ ወደ ማጎሪያና ቦታዎች አስገባ ! ሰጥ** ለጥ **አድርገኽ ተቆጣጠር !** የሚሉ አሰቃቂ መመሪያዎችን ሰጥቷል። የታሪክም ሆነ የህግ፤ የኅሊናም ሆነ የትውልድ ተጠያቂነት አይኖርብህም ! ብሎ ፍጹማዊ ሥልጣን ሰጥቷል ። ገዳዮቹን ሁሉ ሰብዕናቸውን ገፍፎ ወደ አውሬነት ለውጧቸዋል ።

የሰው ልጅ ሰብዕናውን ወደ አውሬነት እንዲለውጥ ከተገደደ ፤ ተቆጣጣሪ ኅሊናውን ስለሚገፈፍ ፤ በገዛ ወገኑን ላይ የሚያቅራራበት ቅላፄ " **እየቆረጠ ሰጠው ላሞራ !** " ነው ። በሀገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ፤ የገደሉትን ሕዝብ ሬሳ እየሸጡ ያለፉ መሪዎችን ሳንረሳ፤ አሁን ደግሞ የዜጎቹን ሬሳ ክምር፤ በጅምላ የሚቅብሩ መሪዎች ተተክተዋል። የዕምነት ሀገር የነበረችውን ኢትዮጵያ፤ ዕምነት አልባ ሰዎች ይገዟታል።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሀገራችን፤ ነፍሰ-ጡሮች ሊኖሩባት አይቻላቸውም ከሚል ዘመን ተደርሷል ። ይኽ ሁሉ መከራና ስቃይ ሊፈፀም ምክንያት የሆነው፤ ወያኔዎቹ፤ በፖለቲካ ሥልጣናቸው ለመቆየት ሲሉ ብቻ ነው። የሀገራችን የመንግሥት ሥልጣን ፍቅር ፤እስከዚህ ድረስ ሰውን ወደ አውሬ የሚለውጥ ከሆነ፤ ሁሉም ዜጋ፤ " ፖለቲካ በፍንጫየ ይውጣ! " ብሎ አመፁን የሚያቆም ይመስላቸዋል። የተጨቆነው ሕዝብ፤ ሁሉንም ነገር ጥብ እርግፍ አድርጎ በመተው፤ አንገቱን ድፍቶ፤ እጁን አጣምሮ፤ ሞራሉን ደፍቶ ፤ ሰጥ-ለጥ ብሎ እንዲገዛ ይገደዳል የሚል ምኞት ወያኔዎቹ ያስተናግድሉ። ሕዝባዊው ዐምጽ ግን፤ አይቆምም። ይኽንን ሀቅ በሚያስተማማን ደረጃ ለማረጋገጥ ሦስት በቂ ምክንያቶች አሉ።

**1ኛ.** ተፍጥሮም ሆነ ሣይንስ እንደሚያረጋግጡት ፤ በአንድ ሀገር ዐብዮታዊ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው፤

አገዛዙ፤ (ሥርዐቱ) እንደለመደው ሕዝቡን ረግጦ ለመግዛት ዐቅምና ቁመና ሲያጣ። መንግሥታዊ ጡንቻው እያዛለ ሲሄድ፤ የውስጥ ውኅደቱና መዋቅሩ እየተፍረከረከ ሲመጣ፤ የመጨቆኛ መሳሪያዎቹ እየዛጉ ሲመጡ፤ አገልጋዮቹ ሲከዱ፤ የስለላ መረቦቹ ሲበጣጠሱ፤ ባላሥልጣናቱ ሲከፋፈሉ ፤ አንዱ በሌላው ላይ ጥርጣሬውን እያጎላ ሲሄድ፤ ዐለቃው በጭፍራው፤ ጭፍራው በዐለቃው ላይ ዕምነት ሲያጣ፤ ሁሉም በየራሱ የግል መውጫውን ማፈላለግ ሲጀምር፤ መናናቅ፤ መኮራረፍ፤

መተማማትና አሉባልታ ሲሰፍን፤ ባላሥልጣናቱ ሲጋጩ ፤ ሲጣሉ ፤ ባለመስማማት ሲፍረከረኩ፤ ሲጠላለፉ ወዘተርፈ .....ነው::. ይኸ ዕውንታ በ 1966 ዓም ሕዝባዊ ዐመፅ ተረጋግጧል። የማይሻር አሸራውንም አትሞ ሄዷል። ዛሬም መደገሙ አይቀሬ ነው።

በመጨረሻው ወቅት የሕዝቡ ትግል አቸናፊ መሆኑን የተረዳው የሥርዓቱ ደጋፊ ሁሉ፤ የድል አጥቢያ ሠልፍ ለማሳመር ወያኔን እየከዳ እንደሚመጣ ማንም ሊጠራጠር አይገባውም። ጥቅመኛ ለጥቅሙ ሲል ሠልፉን ማሳመሩ አዲስ ነገር ስለማይሆን፤ ወያኔን አውግዞ የሚመጣውን ከማስበርገግ ይልቅ፤ በአግባቡ መያዝና መጠቅም ፤ ከብልኅነት የራቀ አመለካከት ነው ሊባል አይችልም። ባንዳው ሁሉ ተገልብጦ ሲመጣ፤ ለአዲሱ ሁኔታ ታማኝነቱን ለማስመስከር ሲል፤ የማይፈነቅለው ድንጋይ፤ የማይበጥሰው ቅጠል አይኖርም። " ሎሌ፤ በአፍላው ፤ የአህያ መዥገር ይከላል! " የሚባለውን ተረት እንገነዘባለን።

የዚኸ ሁሉ ድምር ውጤት ፤ ሥርዓቱ እንደ ሥርዓት፤ መንግሥቱም እንደ መንግሥት ሥልጣንና ኃይል ማጣት ይሆናል ። ገዥና ተገዥ ፤ መሪና ተመሪ ይጠፋና፤ ክፍተት ተፈጥሮ፤ ምስቅልቅል ቦታውን ይይዛል። የሥርዓቱ ተጥቃሚዎች ሆኑ፤ የአገዛዙ ደጋፊዎች ቀስ በቀስ መከዳት ይጀምራሉ ። እነ ኃይለማርያም፤ በእነ ተስፋ ማርያም፤ እነ ጫልቱ፤ በእነ ማሚቱ ይተካካሉ ። ይኸ ሁኔታ፤ ዛሬ ወያኔ ያለበትን ተጫባጭ ሁኔታ ይገልጸዋል። በመገለባበጥ፤ በመሸጋሸግና በመተካካት፤ የሀገሪቱ ስር የሰደደ ችግር አይፈታም ።

ወቅታዊው የህዝብ ጥያቄ፤ የባላሥልጣናት ልውውጥ ወይም ደግሞ የመንግሥት ቅያሬ ሳይሆን፤ ስር ነቀል የሆነ የሥርዓት ለውጥ ነው። ምን ዓይነት ለውጥ ? የሚለውን ጥያቄ መመለስ የሚችለው፤ ለውጥ ፈላጊው ሁሉ እንደሆነ ማወቅ አለበት ! በሚገባ ሳይዘጋጁ፤ ተጠናክረው ሳይሰናዱ፤ መተኪያ አማራጭ መሆን አይቻልም። የ 1966ቱ የካቲት ድክመት ዛሬ በ2010 ዓም የካቲት እንዳይደገም እናሳስባለን!

የወያኔ አባላት ሁሉ፤ አንዱ ሥልጣኑን እየለቀቀ፤ ሌላው የተለቀቀውን ሥልጣን ለማያዝ ሲያቋምጥ፤ የመተንፈሻ ጊዜ አግኝታልናል ብሎ ሁሉም ራሱን ያታልላል። የሥርዓቱ አራማጅ ሁሉ፤ በዚህ ግርግር፤ የመተንፈሻ ዐየር ለመተንፈስ ፤ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ይረዳኛል ብሎ ይመኛል ። ሕዝባዊ ዐመፁ ግን ይቀጥላል። አገዛዙ በቆየ ቁጥር መቃብሩን በጥልቀት ከመቆፈር በቀር ፋይዳ አይኖረውም ። "ሢራክ በመግባሩ ጠፋ መቃብሩ " ይሆንና ታሪኩ ፤ በዐርዮስ ታሪክ ይደመደማል።

ሰማይ ምድሩ የተደፋበት ወያኔ ፤ ዛሬ፤ የልብ ወዳጆቹ የነበሩት ፤ እነ ሄርማን ኮኸን፤ እነ ዴቪድ ሽንና ሌሎቹም፤ ፊታቸውን አዙረውበታል ። ምዕራባውያን የበላይ ጠባቂዎቹ፤ በውስጥና በውጭ ማስጠንቀቂያ፤ ግፊትና ተፅዕኖ እያጣደፉት በመምጣት ላይ ይገኛሉ። የቱኒዝያው ቤን አሊ፤ የግብፁ ሁስኒ ሙባረክ፤ የሊቢያው ሙዓመር ኻዛፊ ፤ ዕድል የሚገጥመው መሆኑን በሚገባው ቋንቋ እየነገሩት ነው። **" የሚያዋጣህ መንገድ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መታረቅ ብቻ ነው ።:"** ብለውታል። አዝዘውታል። የኋላ ኋላ ትዕዛዛቸውን መፈፀሙ ባይቀርም፤ ለጊዜው ግን " ያደቆነው ጋኔል ሊላቀቀው አልቻለም ። ሊያላቅቀው የሚችለው ፤ የተባበርውና የተቀጣጠለው የመላው ሕዝብ ትግል ብቻ ነው።

ቢሆንም ቅሉ ፤ **" ወያኔ ሊወድቅ አንድ ሐሙስ ቀርቶታል! "** የሚል ማቋመጥና መዘናጋት አይገባም። ትግሉን በሁለንታነዊ ገፅታው ከማፋፋም በስተቀር መዘናጋት በሕዝቡ ተነሳሽነትና ርብርቦሽ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንደመጨመር የቆጠራል ። ያልተቋረጠ ትግል፤ የድል ዋስትና መሆኑን መዘንጋት አይቻልም ! የግብር -ይወጣ ሙከራ፤ ፋይዳ- ቢስ ነው።

**2ኛ.** በጭቆና አገዛዝ ቀንበር ሲማቅቅ የቆየ ሕዝብ ፤ቀንበሩን መሸከም ሲያቅተው፤ አልገዛም ብሎ አምፆ ሲነሳ፤ ከፍርሃት ቆፈን ሲላቀቅ፤ ድፍረት አግኝቶ አደባባይ ወጥቶ ተቃውሞውን ሲገልፅ፤ አስፈሪውን ሥርዓት በድፍረት ሲጋተረው፤ የተቃውሞው አድማስ ሀገራዊ ስፋት ሲያገኝ ፤ በዐመፁ ምክንያት ገዥዎች እንደ ቀድሞ በሰላም የማይኖሩበት ሁኔታ ሲፈጠር ፤ ፀጥታ ሲደፈርስ ፤ ሥርዓቱ የመሰረተው ህግና ደንብ የሚያከብረውና የሚፈራው ሲጠፋ ፤ ምልዐተ-ሕዝቡ በራሱ መንገድና አካሄድ የየግል ርምጃ ለመውሰድ ሲገደድ፤ ወዘተርፈ ነው።

ይኽ እንዳለ ሆኖ፡-----

ሀገርን፤ ሀገር የሚያስብሉት ሦስት መሠረታዊ ምሰሶዎች እንዳሉ መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል ። ሦስቱ ምሶሶዎች፤ አንድም ሦስትም ናቸው ። እነርሱም 1.መልከዐ- ምድር፤ 2. ሕዝብና 3. መንግሥት መሆናቸው ነው። ሁሉም ተብባረው ቆመው ሲታዩ፤ አንድ ሀገር ( ) ሀገር የሚያሰኛትን መስፈርት አሟልታ በመገኘቷ ልዕልናዋንና ኅልውናዋን የማስከበር ቁመና ይኖራታል ። እነዚህ ሳይሆኑ ይቀሩና፤ ሀገራዊ ማንነት፤ ውኅደትና የጋሪዮሽ መለያቸው ተደብዝዞ፤ በማንነት ዕውቅና ፍለጋ ይርመሰመሳሉ። የሦስትዮሽ ባኅርያቸው ሳይፀርስ ይቀራል ። ወያኔ እንደ መንግሥት አይቆጠርም።

የሚያውቀው/ ፤የሚያከብረውና፤ የሚፈራው፤  ሕዝብ የለም። በአንፃሩ ግን፤ እንደ መንግሥት የማያውቀው፤ የማይፈራውና  የማያከብረው ሕዝብ ብቻ እንደ ባዕድ አግልሎ ፤ በዐይነ-ቁራኛ ይመለከተዋል ።  ተጠልቶ የተናቀ፤ ማንም ሳያከብረው ራሱን በራሱ ያዋረደ፤ በቃን ! ሂድልን ! ከጫንቃችን ውረድልን  ተወገድልን ! ጥፋልን ! ተብሎ የተወሰነበት ቡድን ነው።  ፍቅር ከሌለ ትዳር እንደማይሳካ ሁሉ ፤ ሕዝብ የጠላው  መንግሥትም  ዕድሜ ሊኖረው አይችልም።   ወያኔ መጠላቱን በማወቁ ነው የአስቸኳያ ዐዋጅ የሚያግተለትለው  !

"  የበሰበሰ ዝናም አይፈራም "ይሆንና፤ ለአለፉት ሃያ ሰባት ዐመታት ብሄር -ተኮር በሆነ  ቅኝት፤ በዘረኞች ፕሮፓጋንዳ ሲታመስ የቆየው ኅብረተሰብ፤ ወደ አንድ ሀገራዊ ዕሴት ለመምጣት ይቸግራል ቢባልም ፤ የኋላ ኋላ ግን ኢትዮጵያዊነት ነጥሮ ሲወጣ፤  ኢትዮጵያውያን  በአቸናፊነት የድል አክሊላቸውን መላበሳቸው አይቀሬ ነው፡፡ ሕዝብ መሥዋዕት ከፍሎ ነፃነቱን  መጎናፀፉ ፤ ሳይታለም የተፈታ ሀቅ ነው።

ዕርግጥ፤ዜጎች ሀገራቸውን ከማፍቀራቸው የተነሳ፤  በወቅቱ ኢትዮጵያ ከወደቀችበት የሕልውና ጥያቄ የምትድንበት መንገድ ያሳስባቸው ይሆናል ። ይኽ መሆኑ ደግሞ ሊያስገርም አይገባውም።  ከልብ የሚያፈቅሩትን ነገር፤ ከፉ እንዳያገኘው መጨነቅና መንሰፍሰፍ የአለና የሚኖርም በመሆኑ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ሀገሩ ያለችበትን የህልውና ጥያቄ ጉዳይ እንዲሁ በአርሞ አይመለከተውም። አይከፍሉ መሥዋእት    እያከፈለ የሚታገለውም ለዚሁ ነው።የትግሉ ጥንካሬ ምን ያህል አርበትባች እየሆነ በመምጣቱ፤ ወያኔዎቹ የአስቸኳይ ዐዋጆቹን በተደጋጋሚ እንዲያዉጁ ምክንያት ሆኗል።  ዐዋጅን በዐዋጅ  መሻር የተለመደ በመሆኑ፤ የወያኔ አስቸኳይ  ዐዋጅ ጋጋታም በሕዝቡ ቆራጥ የትግል ዐመፅ መደምሰሱ አይቀርም።  ለዚኽም የሚከተሉትን  ነባራዊ  ኩነቶች እንደ ማጠያቂያ ምርኩዝ መጨበጥ ይቻላል።

**1ኛ.** ሕዝባዊው ዐመፅ  በመላው የሀገሪቱ ክፍል ዳር -እስከዳር ተቀጣጥሏል። ማንም ኃይል ሊያቆመው አይችልም።

**2ኛ.** ያስቸኳይ ጊዜ ዐዋጁ ፤ የሥርዓቱን መውደቂያ እንጅ፤ የሥልጣን ጥንካሬውን የሚያሳይ አይደለም።

**3ኛ.** የኃይል ሚዛኑ፤ ወደ ሕዝባዊው ዐመፅ እያጋደለ በመሄድ ላይ እንደሆነ ምልክቱ፤ ወያኔ በመከላከል፤ ሕዝባዊው ዐመፁ በማጥቃት ደረጃ መሆኑን ያሳያል። ዐመፁ እያገለ፤ ሥርዓቱ ፤ እንደ በረዶ ክምር እየቀለጠ መሄዱ፤ የሕዝቡን ትብብርና ቁርጠኝነት ማረጋገጫ ሆኗል ። የኃይል አሰላለፉ፤ በፃዕረ-ሞት በሚፈራገጠ አገዛዝና ዕለት- በዕለት እየተጋገለ በሚገሰግሰው ሕዝባዊ ዐመፅ መካከል ነው። የመጨረሻው አቸናፊ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚሆንም ጥርጥር አይኖርም ።

**4ኛ.** የወያኔ ባዕዳን ደጋፊዎቹ፤ በዘላቂ ጥቅማቸው ላይ ስለሚያተኩሩ ፤ ድጋፋቸውን እያሳጡት መሄዳቸውን ምልክቶች አሉ። ሁኔታው እየተባባሰ ሲመጣ ፤ የትላንቷ ሶቬየት ኅብረት መሪ የነበረው ሚካኤል ጎርባቾቭ ደርግን እንደከዳው ሁሉ ፤ ዛሬ ምዕራባውያኑም ፤ወያኔን እንደሚከዱት የቅርብ ትዝታችን ያስታውሰናል ። " ቀን ሲከዳ፤ ሁሉም ይከዳል" ።ሕዝባዊው ዐመፅ ሲጠናከር፤ ሰማይ ምድሩ ይሸሻል ። ይደፋል። ይከዳል፡፡ ጥቅመኛው ሁሉ ጓዙን ይዞ ይፈረጥጣል። መውጫ-ቀዳዳ ይጠፋል። የአፍ ወዳጁ ሁሉ ይከዳዳል። የመተዛዘብ ወቅት ይሰፍናል። መርኀና ኀሊና ለክህደት ቦታቸውን ይለቅቃሉ። ሁሉም ግን፤ በህዝባዊው ዐምፅ አቸናፊነት ቦታ ቦታውን መያዙ አይቀርም ።

**5ኛ ሁለቱ የሀገሪቱ ታላላቅ ብሄሮች፤ ኦሮሞና ዐማራ፤ አንድ ላይ ተበብረው በግንባር -ቀደም ብቻ ሳይሆን በአስተማማኝ ደረጃም ዐመፁን እያቀጠተሉት ይገኛሉ። " የከፋፍለህ ግዛ " ተንኮል እንጦሮጦስ ገብቷል ።**

ከአንድ እስከ አምስት ተራ ቁጥር የሰፈሩት ዕውነታዎች የትግሉ ጥንካሬዎች መሆናቸው ባይዘነጋም ፤ የሕዝባችን ትግል ለድል እንዲበቃ ግን በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ተስማምተን ኃይላችንን አስተባብረን ከመታገል በላይ ከውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ነጻ በሆነ ሁኔታ የአገራችንን መጻኢ እድል ፤ በስምምነትና በአንድነት የሚወስንበት ሁኔታ ማመቻቸት አለብን።

ከላይ የተጠቀሰውን እውን ማድረግ ቀልል ባይሆንም፤ የወያኔን አስቸኳይ ዐዋጅ እየሰበሩ መታግል ግን ለድል መብቃት፤ የመጀመሪያው በር ከፋች ነው።

ዐዋጁን በማፅ እያንኮታኮቱ መደምሳስ የማይቀር ዕውነታ ነው !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !